# የዕለት ሲሳይ

በሳን ሆዜ ካሊፎርኒያ የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ጎብረት የሚታተም
ወርሃዊ የጥሞና ጊዜ መመሪያ

## አዘጋጆች

ሰይፉ ኢብሣ
እበበ ተፈራ
ዶ/ር ግርቆስ ዘመደ
ሣራ ደበበ
ፍሲሐ አጥላው

## የሥነ-ጽሑፍ አስተዋጽዖ

አቶ ዓለም ባዘዘው
አቶ መለሰ ወጉ
መና መጽሔት (ከአ.አ. ሰፈረ ገነት ቢ/ክ )

☎ (408)266-9242

ያለ ቤተክርስቲያኒቱ ፈቃድ መልሶ ማሳተም ክልክል ነው

የንበብ ክፍል ኤር 16 19

# የሚችለው አስቻለኝ

የለው ህይወት በመጠበቅ የተሞላ ነው። ሕጻን ልጅ አድጎ እንደ ታላላቅ ወንድሞቹ ብለክሊት ለመንዳት፣ የህክምና ተማሪውም የረጅም ዘመን ትምህርቱን አገባዶ ሀኪም የሚሆንበትን ቀን ይጠብቃል። ወጣቱ የሚወዳትን አግብቶ በአንድ ጣራ ሥር አብረው የሚኖሩበትን ቀን በናፍቆት ይጠብቃል። ለው የሚፈልገውን ለማግኘት «መታገሥን» መማር አለበት።

ለው መታገስ ያለበትን የጊዜ ክልል ከወቀ ምንም ያህል ጊዜው ቢረዝምም ታግሶ መጠበቅ ይችላል። አንዳንድ ውብ የሆነ መንፈሳዊ ሕይወት ያላቸው ሰዎች ላያስቡት ድንገት ሥጋቸው በደዌ ተመትቶ ሲሰቃዩ ይታያሉ። ከእነዚህ መከከል አሜሪካ ውስጥ ኮልጌት ዩኒቨርስቲን ከአቋቋሙት ሰዎች መከከል አንደኛው ዶክተር ናትናኤል ኬንድሪክ ይገኙበታል። እኒሁ ለው ገና በአፍላ ዘመናቸው በልታወቀ በሽታ ተመትተው ከአልጋ መውረድ የማይችሉ ሽባ ሆኑ። ዶክተር ኬንድሪክ ውብ የሆነው የክርስትና ሕይወታቸው በፈታቸው ገጽታ ይታይ ስለነበር አንዳንድ ጊዜ ከአማልክት መከከል የወጡ ይመስሉ ነበር። አንድ ቀን ልጃቸው ከተኙበት ጠጋ ብሎ «አባዬ አሁን የምወድህን ያህል ከዚህ በፊት ወድጄህ አላውቅም፣ ምን አለ የአንተን መከራና ስቃይ እኔ መሸከም በቻልኩ ኖሮ!» አላቸው። እኝህም አባት ለልጃቸው ሲመልሱ «ልጄ ሆይ! ሌላ ተጨማሪ ስቃይ የለኝም፣ ያለኝን እርሱ ተሸክሞታል። በስቃይ ውስጥ እንዳልፍ የፈቀደው ጌታ አንተ ከምትወደኝ የበለጠ ይወደኛል፣ ለእኔ የሚበጀውን ከማንም ለው የበለጠ ያውቅልኛል። አንዳንድ ጊዜ ደስታ የሞላበት ሕይወት ያላለፍኩት፣ በህመም አልጋ ላይ ከዋልኩበት ጊዜ ጀምሮ እንደሆነ ይለማኛል። ምህረቱና ጸጋው ለእኔ ለፊ ነው» ሲሉ መለሱለት።

አንድ ጸሀፊ ሲናገር «እግዚአብሔር የማያውቀው «ይሁን» ያላለው ሃዘን አይደርስብንም፣ እያንዳንዷ የፅንባ ጠብታችን በእርሱ የተቆጠረች ነች፣ ከወለነው በላይ አይፈስም። በኃይል ቢፈስ እንኳን የእርሱ ፈቃድ አለበት ብለን እንቀበል። እንዲህ ከሆነ እያንዳንዷ መራራ የፅንባ ጠብታችን በክርስቶስ ዓይን ፍጹም ግሩምና ድንቅ ሆና ትታያለች»አለ።

ወገኖቼ! ያለፋችሁበትን ህይወት ወደኋላ መለስ ብላችሁ ስታዩት እንዴት ታግሼ አለፍኩት ብላችሁ ጠይቃችሁ ይሆን? ምስጢሩ ጌታ ስለደገፋችሁ ነው። የማይቻለውን እንዲቻል የሚያደርግ እርሱ ብቻ ነው።

ጸ ሎ ት ጌታ ሆይ የማይቻለውን እንድችል አስችለኝ።

የንባብ ክፍል ማቴ 25 34 36

## እያየሁት ያላወቅሁት

ኢየሱስ በምድር በነበረበት ዘመን በቤታቸው በመንደራቸው የተቀበሉት ጀልባቸውን ያዋሱት የመቃብር ቦታቸውን የሰጡት ምንኛ ዕድለኞች ናቸው ብለን ማሰባችን አይቀርም። በዘመናችን አሁንም ያ ኢየሱስ እንደ ገና ብቅ ብሎ በአደባባያችን ቢመላለስ ወደ ቤታቸው የሚጋብዙት ሰዎች ቁጥር ትንሽ እንደማይሆን እገምታለን። ይሁን እንጂ ኢየሱስ በጠበቅነው ዓይነት ሳይሆን በረሃብ ፊቱ ጠውልጎ ማደሪያና መጠጊያ አጥቶ መጻተኛና ስደተኛ ሆኖ ሲንከራተት ይታያል።

ወራቱ የክረምት ወራት በመሆኑ ብርዱ ሥጋንና አጥንትን ለነጣጥቆ ወደ ውስጥ ዘልቆ በሚገባበት በተለይ በእንድ ምሽት እንድ ራቪያዊ ወታደር የምሽቱ የዘብ ተረኛ ሆኖ አከባቢውን ይጠብቅ ነበር። ይሽው ወታደር ብርዱን ለመቋቋም ሰውነቱን ለማፍታታት ወድያና ወዲህ ሲመላለስ እንድ ድሃ የቀን ሠራተኛ ከሥራው ወደ ቤቱ ሲሄድ አየውና በጣም አዘነለት። ጠጋ ብሎ ብርዱን ሳይፈራ የለበሰውን ኮት አውልቆ ከለበሰው በኋላ «እኔ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ቤቴ እደርሰለሁ፤ አንተ ግን ሌሊቱን ሙሉ ብርድ ላይ ስለምትቆም በመጠኑም ቢሆን ብርዱን ይከላከልልሃል» አለው።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ያ በጎ አድራጊው የቀን ሠራተኛ በኃይል ታመመ። ከመሞቱ ጥቂት ቀናት ቀደም ብሎ ራዕይ ያይ ነበር። በራዕዩም ውስጥ አዳኙን ኢየሱስ ክርስቶስን ማየት ጀመረ። በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ለብሶት የነበረው ከዚህ በፊት እርሱ ይለብሰው የነበረው ኮት እንደነበረ አስታወሰ። ኢየሱስንም « ያ የሰበሰከው ኮት የእኔን ኮት ይመስላል » አለው። ኢየሱስም «ታስታውሳለህ እንድ በጣም ብርድ በሆነበት ምሽት በጣም እንደበረደኝ አይተህ ኮትህን አውልቀህ እንደሰጠሽኝ?» ሲል ጠየቀው። ያም ድሃ ሰው «ለአንድ ወታደር ኮቴን አውልቄ እንደሰጠሁት አስታውሳለሁ፤ ቢሆንም ያ ሰው እንተን አይመስልም» አለው። ኢየሱስም ፈገግ ብሎ «ከእነዚህ ከወንድሞቼ እነስተኛ ለሆነው ለእንዱ እንኪ ያደረግኸው ሁሉ ለእኔ እንዳደረግኸው ነው» አለው።

ለድኾች ያሳየነው ቸርነት ለኢየሱስ እንደ አደረግነው መሆኑን አለቀድመን አውቀናልና «ጌታ ሆይ! ተርበህ ወይም ተጠምተህ ወይም ታርዘህ ታመህ ወይም ታስረህ መቼ አየንህና ለንረዳህ ቀረን?» በማለት ምክንያት መስጠት ስለማንችል እጆቻችን ደከሞችን ለመርዳት የተዘረጉ ይሁኑ።

ጸ ሎ ት ጌታ ሆይ ደከሞችን ማየት እንድችል ዐይኖቼን ከፈትልኝ።



የንባብ ክፍል ዮሐንስ 3 18

## የማይታየው ታየኝ

ሁላችንም መንግሥተ ሰማይ የት እንደሆነ ምን እንደሚመስል የማወቅ ጉጉት አለን። የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ የሚጠብቁና ኢየሱስንም በማመን የሚጸኑ ቅዱሳን ያንን ማየት ስለሚችሉ ዕድለኞች እንደሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። (ራዕይ 14 13)።

እንድ ጊዜ እንድ የቤተ ክርስቲያን መጋቢ ስብከቱን ወርሶ ከመድረኩ ሲወርድ እንድ ምዕመን ቀረብ ብሎ «ዛሬ ስለ መንግሥተ ሰማይ ግሩም የሆነ ትምህርት ነው የሰጠኸን ግን የት እንደሚገኝ አልነገርከንም» አለው። መጋቢውም «እዝናለሁ!የት እንደሚገኝ ትክክለኛ ቦታውን ልነግርህ አልችልም፤ ምን ዓይነት እንደሆነ ግን በቅድሚያ እንድትቀምሰው ላደርግህ እችላለሁ» አለው። ሰውየውም በጉጉት «እንዴት ልታለየኝ ትችላለህ? ሲል መልሶ ጠየቀው። መጋቢውም ከዚያ ፊት ለፊት ከሚታየው ኮረብታ ላይ የምትኖር የቤተ ክርስቲያናችን አባል የሆነች እንዲት በጣም የታመመች ሴት አለች። በህመም የአልጋ ቁራኛ ከሆነች ብዙ ወራቶች አልፈዋታል። ሁለት ልጆቿም ታመው ተኝተዋል። የሚመገቡት በቂ ምግብ የላቸውም፤ የሚሞቅ የብርድ ልብስ ያስፈልጋቸዋል። ቤታቸውን የሚያሞቁበት በቂ እንዉትም የላቸውም፤ አንዳንድ ነገር ይዘህላቸው ሂድና ሴትየዋንም «የእኔ እህት እነዚህን ነገሮች በኢየሱስ ስም ይዝልሽ መጥቻለሁ» ብለህ ማድረግ የምትችለውን አንዳንድ ነገር እድርግላቸው። ከመውጣትህ በፊት መጽሐፍ ቅዱስ አንብብላቸውና ተንበርክከህ አብረሃቸው ጸልይ። ይህን ስታደርግ መንግሥተ ሰማይ የገባኸውን ያህል ደስታ ከልተሰማህ ንገረኝ፤ እኔ ያወጣኸውን ወጪ ሁሉ እከፍልሃለሁ» አለውና ተለያዩ። በማግስቱ ያ ሰው መጋቢውን አገኘውና «ያንን ትንሹን መንግሥተ ሰማይ ገብቼ እየሁት ግማሽ ሰዓት ያህልም ቆይቼ ወጣሁ» አለው።

ወገኖቼ እኔና አናንተም የማይታየውን ማየት የምንችለው ኢየሱስ በምድራዊ አገልግሎቱ ልዩ ትኩረት ሰጥቶለቸው ለነበሩት ድሆች ረዳት የሆንን እንደሆነ ነው። ይህን ለማድረግ በለ ብዙ ብር መሆንን አይጠይቅም። ከሎምበስ ወርቅ አልነበረውም፤ ሌላው ቀርቶ ሰተራበ ልጁ እንጀራ እንደልቡ ሳያገኝ ሞተ፤ ይሁን እንጂ አዲስ ዓለምን በማግኘት ሰብዙዎች በረከት ሆነ። እኛም የማይታየውን መንግሥተ ሰማይ ለማየት ብንፈልግ፤ ደከማውን ለማገዝ የምንችለውን ሁሉ እናድርግ።

ጸ ሎ ት
እግዚአብሔር ሆይ የማይታየውን ማየት እንድችል ዐይኖቼን ከፈትልኝ።

የንባብ ክፍል ዕብ 13 6

## የማለየው አየኝ

መልስ ልናገኝሰት ያቃተን አልፎ አልፎ አንዳንድ ጥያቄ ወደ አዕምሮአችን መምጣቱ አይቀርም። በተለይ የምናልፍበት መንገድ ጠባብና ዉስጣ ሲሆንብን የእግዚአብሔርን ድምጽ ከምንጊዜውም የበለጠ መስማት በምንፈልግበት ወቅት ድምጹ ሲርቀን «አጠገቤ እያሰ ማየት እቅቶኝ ነው? ወይንስ እግዚአብሔር ሆነ ብሎ ተደብቆ ነው? ብለን መጠየቃችን አይቀርም። ይሁን እንጂ እኛ ማየት ስላልቻልን ብቻ እግዚአብሔር በአስፈላጊው ወቅት አይደርስልንም ወይንም አይገኝም ማለት አይደለም።

የኢየሩሳሌም ጳጳስ የነበሩት አቡነ ጋበት ከብዙ ዓመት በፊት ኢትዮጵያ ውስጥ ሚስዮናዊ ሆነው ሲያገለግሉ በአገልግሎታቸው ምንም ዓይነት ፍሬ ማየት በለመቻላቸው እጅግ በጣም ያዝኑ ነበር። ሁሉ ሰው በእርሳቸው ላይ በጠሳትነት የተነሳቸቸው ሌሳው ቀርቶ አግዚአብሔር እንኪን የተደበቀቢቸውና የሸሸቸው የመሰላቸው ጊዜ ነበር። ልቢቸው በሀዘንና በጭንቀት ተሞልቶ ከጌታ ጋር በጸሎት ለመነጋገር ወስነው ምንም ዓይነት የብርሃን ጭላንጭል ከማይታይበት አንድ ዋሻ ውስጥ ገቡ። በረጅሙ የጸሎት ጊዜያቸው እግዚአብሔር ፍጽም የረሳቸውና የጣሳቸው መሆኑን በመግለጽ ልቢቸውን ከፋፍተው በእግዚአብሔር ፊት እንቢቸውን አፈሰሱ። በዚያ ፍጹም ብርሃን በሌለበት ዋሻ ውስጥ ረጅም ጊዜ በመቆየታቸው ወሰማውን ተለማምደውት ነበር። ዓይናቸውን ገለጥ አድርገው ያንን ዋሻ ዙሪያውን ሲቃኙ አንዲት በረሃብ የጠወለገች ጅብ ከነግልገሎቿ ተቀምጣ አዩ። ጅቢ በቅርቡ ከወለደቻቸው ግልገሎቿ ጋር ስትሆን ልጆቿን ሊነከቢት የመጣ ጠሳት ስለሚመስሳት በአከባቢዋ ተንቀሳቃሽ ነገር ስታይ ያንን ቶሎ በማጥቃት ከአራዊት መከከል የሚወዳደራት እንደሌሰ የታወቀ ነው። ይሁን እንጂ አቡነ ጋበትን እግዚአብሔር ይጠብቃቸው ስለነበረ ያቺ የተራበች ጅብ ልትተናከሳቸው አልቻለችም ነበር። «የእግዚአብሔር እጅ በእኔ ሳይ መከራ ለማድረስ ተዘርግቷል» ብለው በሚያስቡበት ወቅት ያኔ ያ የእግዚአብሔር እጅ የዚያችን የተራበች ጅብ አፍ ለመዝጋት በተግባር ሳይ ነበር። አቡነ ጋበት ይህንን ሲያዩ እግዚአብሔር ፍጹም እንዳልረሳቸውና እንዳልተዋቸው በመረዳት ተጽናንተውና ደስ ብሎአቸው ከዚያ ዋሻ ውስጥ ወጡ።

ወገኖቼ እኔና እናንተም እግዚአብሔር መንፈሳዊ ዓይናችንን ቢከፍትልንና ብናይ በተለይ ያለንበት ሁኔታ ከብዶብን «እግዚአብሔር ትቶኛል እግዚአብሔር ረስቶኛል እግዚአብሔር ለእኔ ፍጹም ግድ የለውም» በምንልበት ወቅት እግዚአብሔር ድብቅ ከሆኑ አደጋዎች ሁሉ ምን ያህል እንደጠበቀን ማየት በቻልን ነበር።

ጸሎት

ጌታ ሆይ ጥበቃህን አይ ዘንድ አይናቼን ክፈት።



የንባብ ክፍል ኢዮብ 40፡ 3 5

## ዓይኔ አየችህ

« እነሆ እኔ ወራዳ ሰው ነኝ፡ የምመልስልህ ምንድር ነው? » (ኢዮብ 40 4)

ከእግዚአብሔር ጋር ተከራክሮ ያሸነፈ ሰው የለም ሲኖርም አይችልም። እርሱ የሚያደርገውን የሚያውቅ ጻድቅ ፈራጅ ስለሆነ ስለምን ፍትህ ጎደለ፡ ለምን ይህ እንዲሆን ፈቀድህ ልንለው አንችልም።

እግዚአብሔር ኢዮብን በውኑ የሚከራከር ሰው ሁሉን ከሚችል አምላክ ጋር ይከራከራልን? ብሎ በጠየቀው ጊዜ የሚናገረው ነገር አልነበረም። እግዚአብሔር በተናገረ ጊዜ ኢዮብ ወራዳ መሆኑን ተገነዝበ የሚመልሰው ነገርም እንዳልነበረ ተረዳ፡ ይህም ብቻ እይደለም የእግዚአብሔርን ማንነት አወቀ ሁሉን ያደርግ ዘንድ የሚችል እንደሆነ ሃሳቡንም የሚከለክል እንደሌለ አወቀ።

ኢዮብ እግዚአብሔርን በሰው በኩል ሰይሆን አሁን ያወቀው በማየት ነው። በቅርብ ሆኖ አነጋገረው በግሉ ሲያውቀውና ሁሉን ቻይ እንደሆነ ሲረዳ እራሱን ናቀ፡ ተጸጸተም፡ የእግዚአብሔርን ድምፅ በሰማ ጊዜ ያየው የተመለከተው የእግዚአብሔርን ታላቅነትና የእራሱን ታናሽነት ነበር። እግዚአብሔር አምላክን በሚገባ ሰናየው አሰራሩን አንጠራጠርም ይልቁንም አንተ ታላቅ ነህ እኔ ግን የተዋረድሁ ነኝ እንሰለን። ይህንን ስንገነዘብ እግዚአብሔር ለኢዮብ ምርከውን እንደመለሰ እንዲሁም ለእኛ ምርከአችንን ይመልስልናል።

ምንም እንኪ ኢዮብ ያለ ዕውቀት ቢናገርም በቅንነት ስለተናገረ እግዚአብሔር ቅንነቱን ወደደ አከበረውም ያጣውን ነገር ብቻ ሳይሆን በእጥፍ አብዝቶ ለጠው፡ ዕድሜንም አጠገበው። በእርግጥ ከተፈተነ በኋላ እንደ ወርቅ ወጣ።

እግዚአብሔር ምርከህን እስኪመልስልህ ድረስ በፈተናህ ሁሉ እየታገስህ ፍጹምነትህን ትይዘለህ? ይህንን ለማድረግ አንተ ፈቃደኛ ከሆንክ እግዚአብሔር የሚያሰችል ጸጋውን ይሰጥሃል።

ጸ ሎ ት

የእጆችህን ሥራ ዓይኔ እያየች አምላክ የለም እንዳልል ጠብቀኝ።

የንባብ ክፍል ማቴ 6 25 33

## ጭንቀትን ማስወገድ

« አትጠነቁ »ማቴ 6 25

በዓለም ታሪክ ውስጥ በጀግንነቱና በድል አድራጊነቱ ይታወቅ የነበረው ታላቁ እስክንድር አንድ ቀን በግዳጅ ላይ ያሉትን ሠራዊት በምሽት በየድንኳናቸው እየዘረ ጉብኝት ያደርግ ነበር። በዚያን ምሽት እንዱ ወታደር በጦርነት ሜዳ ውስጥ ሆኖ ገና በሃገሩ በቤቱ ሳለ የተበደረውን የብድር ዝርዝር እየጻፈ ከደመረ በኋላ የዕዳውን ትልቅነት በመረዳት እያሰበ በመጠነቅ፡ ሚስቱና ልጆቹ የሚጠብቃቸውን በርነት እያየ ልቡ ከብዶት ሳለ የብድሩን ዝርዝር እጻፈበት ላይ « ይህንን ዕዳ ማን ይከፍልልኛል? » ብሎ እንደጻፈ እንቅልፍ ሸለብ አድርጎት ተኛ። በዚህን ጊዜ ታላቁ እስክንድር ወታደሩ እተኛበት ድንኳን ገብቶ የጻፈውን የብድር ዝርዝር ተመልክቶ፡ መጠነቁን በመረዳት «እኔ እስክንድር እከፍለዋለሁ » ብሎ ፈርሞበት ሄደ። ያ በጭንቀት የተያዘው ወታደር ከእንቅልፉ ሲነቃ ምን ያህል ደስታ ይሰማው ይሆን!

ዛሬ አብዛኛውን የዓለም ሕዝብ የተማረውን፡ ያልተማረውን፡ ባለጠጋውን፡ ደሃውን ላይለይ ሰላምን በማጥፋት የሚያስቸግር ትልቁ ነገር ጭንቀት ነው።

ዛሬም በኑሮአችን፡ በሕይወታችን በእቅዳችን የሚያስጠነቀን ነገር ከለ ከእስክንድር እጅግ የበለጠው መድሀን፡ ጌታና ንጉሥ የሆነው ሲያቃልለው ዝግጁ ነው። « እርሱ ስለእናንተ ያስባልና የሚያስጠንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉት »(1ጴጥ 5 7)

ጸ ሎ ት አባት ሆይ! በዚህ ሰዓት የሥጋቴ፡ የፍርሃቴ፡ የጭንቀቴ መነሾ የሆነውን ሁሉ ለአንተ አስረክበሰሁ። አሜን!



የንባብ ክፍል « በኋላዩ ያለውን እየረሳሁ በፊቴ ያለውን ለመያዝ እዘረጋለሁ » (ፊል 3 13)

## ወደፊት መዘርጋት

የአንድን አማኝ ሕይወት የሚያጻክሙ፡ ለጌታ ያለውን ፍቅር እንዲቀዘቅዝ ኑሮውን በዓለም ሥርዓት በመምራት በዓለማዊነት እንዲያዝ የሚያደርጉ ብዙ ነገሮች አሉ ከእነዚህም መካከል ያለፈውን አለመርሣት፡ ወደፊት በተሐድሶ፡ በዕምነት አለመዘርጋት ነው።

አዎ ወደፊት ለመዘርጋት፡ ለመራመድ አዲስ ምዕራፍ ለመጀመር እስቀድመን በኋላ ያለውን ልንረሳ፡ ልንተው ይገባናል። በሕይወታችን እንደጥቁር ነጥብ፡ የምንቆጥራቸው፡ ታሪክችንን፡ ስማችንን፡ እትዳችንን አበሳሽተውብናል የምንሳቸው ሁኔታዎች፡ ውድቀት፡ መሰናከል፡ መሸነፍ ፈጽሞ ወደኋላ ልንረሳቸው፡ ልንተዋቸው ይገባል።

እነዚህ በኋላችን ያሉ የኃጢአትን ክስ፡ ፍርሃትን፡ ጥርጥር በማምጣት በፈታችን ከሚጠብቀን ታላቅ ተስፋ በረከትና ድል እንዳያስቀሩን ለውድቀትና ለአሰመሳከት ጎጆ ሠርተን ከመዉነት ከመጠበብ ይልቁንስ ወደፊት በመዘርጋት ከጌታ የተነሣ አዲስ ምዕራፍ፡ርምጃ፡ ዕድቅ በረከት ለመቀበል በቁርጠኝነት ልንነሳ ይገበናል።

አንድ የታወቁ መሪ « አንድ ነገር ሞክሮ ውጤት ማጣት ውድቀት ላይሆን ውድቀት ግን ምንም ነገር አለመሞከር ነው» እንዳሉት እነሆ ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ ያለው ጌታ ወደፊት በመዘርጋት ሁሉን በተሐድሶ እንድንገናኘው ፈቃዱ ነው።

ጸ ሎ ት

ጌታ ሆይ! የተበላሹ፡ ውጤት ያጡ የሚመስሉትን እርምጃዎቼን፡ ጥረቶቼን፡ ግንኙነቶች ሁሉ በእንተ ላይ በመጣል በአዲስ ተስፋ፡ ኃይል ወደፊት እንድነሣ እርዳኝ። አሜን!

የንባብ ክፍል «በትዕግሥት የፀኑትን ብፁአን እንለቸዋለን» (ያዕ 5 14)

## በመከራ መጽናት

ክርስትና የሞራል መጠበቂያ ሕግ፡ ወይንም ለመለያ የምንጠቀምበት የሃይማኖት ክፍል ሳይሆን በክርስቶስ የተመሠረተ የብጽዕና መንገድ ነው። ነገር ግን ይህ የብጽዕና መንገድ ዛሬ ብዙዎች እንደሚያስቡት የምቾትና የተድላ ጎዳና ሳይሆን በፈተናና በመከራ መታገሥን ይጠይቃል።

በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን በመጋቢነት ያገለግል የነበረው «ፖሊ ከርፕ» የተባለው የጌታ አገልጋይ በክርስቶስ በማመኑና የክርስቶስን ወንጌል በመስበኩ ተከሰሰ በዘመኑ በለሥልጣናት ፊት ቀርቦ ክርስቶስንና ጌትነቱን እንዲክድ ተጠይቆ እምቢ ካለ ግን የሚጠብቀውን አሰቃቂ የሞት መንገድ ተነገረው።

ፖሊ ከርፕ በቁጣ፡በንዴት፡ ተሞልተው ደም ተጠምተው ሊያጠፉት ለተነሱት በለሥልጣናት «ወደለማንያ ዐመታት ያህል ጌታዬ ክርስቶስን ስከተል አንድ ቀን አሣዝኖኝ አያውቅም ዛሬ እንዴት እክደዋለሁ?» በማለት ለፈተና ሣይበገር በዕምነቱ ፀና ሕይወቱንም ለጌታው ክብር ሰዋው፡ የብጽዕናውን መንገድም ተጊዘ። እንዴት ያለ ጽናት፡ ትዕግሥት ነው!

አንባቢ ሆይ ዛሬ እንደፖሊ ከርፕ ሕይወታችንን በንጠየቅም ነገር ግን በሕይወታችን በሚያልፈው ፈተና፡ ችግር፡ መከራ፡ ብጽዕና ያለበትን የትዕግሥትን፡ የጽናትን ጎዳና ወይስ በማጉረምረም በተስፋ መቁረጥ ተይዘናል? በለስን የጠበቀ ፍሬዋን ይበላል። ጌታውን የሚጠብቅ ይከብራል(ምሳሌ27 18)።

ጸ ሎ ት

ጌታ ሆይ! በመከራ፡ በፈተና ሳልፍ አንተን ብቻ በመመልከት ረድኤትህን በትዕግሥት እንድጠብቅ አርዳኝ። አ ሜ ን!



የንባብ ክፍል « በአንተ ለምትደገፍ ነፍስ ፈጽመህ በሰላም ትጠብቃታለህ» (ኢሳ 26፡4)

## በእግዚአብሔር መደገፍ

የመጀመሪያ ልጃችን አድጎ በእግሩ መሮጥ መጫወት በጀመረበት ጊዜ ሁሉን ነገር በራሱ ጥረት ለማድረግ ያለው ጉጉት እጅግ ከፍተኛ ነበር። እኛ ልንረዳው ስንፈልግ እንኪን ፈጽሞ ፈቃደኛ አይሆንም ነበር። ታዲያ አንድ ጊዜ በመንገድ ላይ አብረን በእግራችን ስንጊዝ በክንዴ መደገፍን እምቢ ብሎ በእግሩ ለመሄድ፡ ለመሮጥ ሁሉን በራሱ ጉልበት፡ ጥረት ለማድረግ ፈለገ። ብንከለክለው ስላልለማን ተውነው ብዙም ሳይቆይ በመሬት ላይ ወድቆ ስለተጎዳ ድምጹን ከፍ አድርጎ ማልቀስ ጀመረ። የአባቱን ክንድ ተደግፎ ከመሄድ ይልቅ የራሱን ጉልበት፡ ጥረት መርጦአልና ሳያሰበው ወደቀ።

አዎ! እኛስ በሕይወታችን፡ በክርስትና ኑሮአችን ሁሉን በሚችል አምላክ ጥላ ሥር፡ በክንዱ መደገፍን ትተን ሁሉን በራሳችን ጉልበት፡ ጥበብ ለማድረግ ስንቲ ሞክረናል? ከአበታችን ድጋፍ ተለይተን የምናደርገው ሩጫ፡ ጥረት ውጤቱ ውድቀት፡ መሸነፍና መጎዳት ብቻ ነው።

በእርሱ በአምላክችን በመደገፍ የሚገኘውን የሕይወት ለላምና መለክታዊ ጥበቃ ብንለማመድ እጅግ የተሻለ ነው። ለውን፡ ሁኔታን፡ ዕውቀትንና ገንዘብን ራሳችንንም መደገፍ በተለበረ ሸምበቆ የመደገፍ ያህል አደጋ አለው። ጌታ እግዚአብሔር የዘለዓለም ዓምባ ነውና ለዘለዓለም በእግዚአብሔር ታመኑ» (ኢሳ 26፡4)

ጸ ሎ ት

አቤቱ አንተን ብቻ እደገፋለሁ ሌላውን ሁሉ በመተው አንተን አለኝታ አደርጋለሁ። አ ሜ ን!

የንባብ ክፍል ዕብ 13 15

## ም ሥ ጋ ና

እንጀራህን በድኻህ ወይም በፈትህ ወዝ ብላ ተብሏልና፥ መኖር እራሱ ችግር ነው። የኑሮን ችግር ለመወጣት በየጊዜው ዕቅድ እናወጣለን። ነገሮች ሲሳኩልን እግዚአብሔርን ማመስገን ችግር የሚሆንብን አይመስለኝም። ነገር ግን የፈለግናቸውን ነገሮች ማግኘት ሲያቅተን ወይም ያልፈለግናቸው ነገሮች ሲመጡብን ጌታን ተመስገን በማለት ፋንታ እናዝናለን።

ኢዮሳፍጥ የሚገለው የይሁዳ ንጉሥ አንድ ጊዜ እሱ ባለው ጦር ሊቋቋመው የማይቻለው ከፍተኛ ሃይል ያለው የሶስት አገሮች ጥምር ጦር ሊወረው እንደመጣ ለማና ተሸበረ። የገጠመውንም ችግር ለመፍታት ጸም አወጀና በእግዚአብሔር ፊት ቀረበ። በመጀመሪያ የእግዚአብሔርን ባህርያት ለእግዚአብሔር አበሰረ፥ ቀጥሎም እግዚአብሔር ለእስራኤል እስከዚያ ጊዜ ድረስ ያደረገውን በመቁጠር እግዚአብሔርን አከበረ። በመጨረሻም የገጠመውን ችግር አስታውቆ የእግዚአብሔርን ዕርዳታ ለመነ። ይህም የኢዮሳፍጥ አመላለክ እግዚአብሔርን አንዋለዋለው። እግዚአብሔርም ኢዮሳፍጥን አለው አትፍራ፥ ጦርነቱ ያንተ ሳይሆን የእኔ ነው። ሕዝብህን ይዘህ በይሩኤል ምድረ በዳ ፊት ለፊት ውጡና ከጠላቶቻችሁ ጦር ፊት ለፊት ቁሙ። እኔም የማደርገውን ታያላችሁ አለው። ኢዮሳፍጥም ሕዝቡንና መዘምራኑን ይዞ ወጥቶ ዝማሬና ምስጋና ሲጀምሩ እግዚአብሔር በተአምሩ የመጣባቸውን ጦር እንዳልነበረ አደረገው።

ዘሬም ችግር በገጠመን ጊዜ በችግሩ ላይ ከመኖር ጌታ በህይወታችን ያደረጋቸውን ድንቅ ነገሮች እያሰብን በፀሎት ወደፊቱ ቀርበን ስለነዚያም ማመስገን ብንጀምር የእግዚአብሔርን ክንድ እንደገና በችግራችን ላይ እናያለን። ለእግዚአብሔር ሁሉ ይቻለዋል።

ጸ ሎ ት ጌሆይ በሁሉ ማመስገንን አስተምረኝ።



የንባብ ክፍል 2ኛነገ 7 1 20

## ለእግዚአብሔር ሁሉ ይቻላል

«ነገ በዚህ ጊዜ በሰማርያ በር አንድ መስፈሪያ መልከም ዱቄት በአንድ ሰቅል ሁለትም መስፈሪያ ገብስ በአንድ ሰቅል ይሸመታል አለ።» 2ነገ 7 1

እግዚአብሔር በራሱ ላይ ትልቅ እምነት አለው። የገባውን ቃል ኪዳን ሁሉ ያከብራል። በሰው ዓይን የማይቻል የሚመስለውን፥ ወይም ለመሆን ረጅም ጊዜ የሚያስፈልገውን እርሱ በትጽበት የሌለውን ወደ መኖር፥ የማይቻለውንም ወደ መሆን ያመጣል።

በዛሬው የንባብ ክፍላችን አስደናቂ የሆነን የእግዚአብሔርን አሰራር እንመለከታለን። በሰማርያ ታላቅ ረሃብ በገባበት ጊዜ፥ የአህያ ራስና የርግብ ኩስ እንኳ ምግብ ሆኖ በሚሸጥበት ዘመን እግዚአብሔር በኤልሳዕ በኩል «ነገ በዚህ ጊዜ በሰማርያ በር አንድ መስፈሪያ መልከም ዱቄት በአንድ ሰቅል ሁለትም መስፈሪያ ገብስ በአንድ ሰቅል ይሸመታል አለ።»

ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች እንደሚናገሩት በጥጋቡ ጊዜ እንኳ ዱቄት በዚህ በረከሰ ዋጋ አይሸጥም ነበር። ለእግዚአብሔር ግን ሁሉ ይቻላል። የረሃብን ዘመን ወደ ጥጋብ ያውም ታይቶ ወደማይታወቅ የጥጋብ ጊዜ በአንድ ቀን ውስጥ መለወጥ ይችላል። እግዚአብሔር ለሰርያውያን የሰረገላና የፈረስ የብዙም ጭፍራ ድምጽ አሰምቶ ድንኳኖቻቸውን፥ ፈረሶቻቸውን፥ አህዮቻቸውንና ሰፈሩን አንዳለ ትተው አንዲሸሹ አደረገ። በነጋታውም እንደ እግዚአብሔር ቃል መልከም ዱቄትና ገብስ በርከሽ ዋጋ ተሸጠ።

ለማይና ምድርን ለፈጠረ አምላክ ሁሉ ይቻለዋል። እግዚአብሔርም የተናገረውን እንደቃሉ ይፈጽማል። ቃሉ ከሚያልፍ የፈጠረው ለማይና ምድር ቢያልፍ ይቀላልና። ወገኔ እንግዲህ በእግዚአብሔር ተስፋ ቸኑን በሙሉ ኑር። አርሱ ቃሉን ሊፈጽም ይተጋልና በእርሱ ፈጽሞ ተስፋ አትቁረጥ። ያለህን፥ የገበልህን ቃል አንዳች ሳያስቀር በጊዜው ያደርገዋል።

ጸ ሎ ት
ጌታ ሆይ በክንድህ ተስፋ አደርግ ዘንድ በእጆችህም ውስጥ አርፍ ዘንድ አርዳኝ።

የንባብ ክፍል ያዕ 1 12 15

## ም ኞ ት

ምኞት ማለት ዘሬ ያልተቀበልነውን ወደፊት ሰማሸሸል ወይም ዘሬ የሌለንን ነገር ወደፊት እንዲኖረን በመሻት በሃሳብ መወሰድ ነው። ምኞት ግን ዝም ብሎ ከሚዳ አይመጣም። ምኞታችን እኛነታችንን ከፍ ከፍ ለማድረግ ከሆነ ቀደም ሲል ከፍ ከፍ አድርገን ያየነው ሰው አለ ማለት ነው። ምኞታችን እንግዲህ ከዚያ ሰው አኩል የምንሆንበትን ወይም በልጠን ልንታይ የምንችልበትን ሁኔታ መቀየስ፣ ብሎም ያልሆነውን ሆነን በሃሳባችን እራሳችንን ለማየት መሞከር ይሆናል።

እንግዲህ ምኞት የሚጀምረው ከማየት ነው። በመጀመሪያ ከእኛ የተሻሉ አድርገን ደረጃ የሰጠነው ሰው ወይም እኛ ካለን ንብረት የተሻሉ አድርገን የቆጠርነው ንብረት ባየንበት ጊዜ የበታችነት ስሜት ተሰምቶናል ማለት ነው። ይህ ሁኔታ ሰሰይጣን ማጥቃት አመቺ ይሆናል። ከዚህም የተነሣ እኛነታችንን አዋርዶ በመክሰስ ችግራችንን ያባብሰዋል፣ እኛም ከዚህ የሃሰት ክስ የተነሣ ራሳችንን ለማሸሸል የሃሳብ ዕቅድ እናወጣለን። በተሰይም ሃሳቡ በመኝታችን ላይ ሆነን ከመጣ ነገሮች ሁሉ ቀሰል እየሆኑ እየተሳኩ በሃሳባችን ሲታዩን ነርቨቻችን ሁሉ ንቁ ይሆኑና እንቅልፋችን ይጠፋል። ሌሊቱ ሲነጋና ከአልጋችን ስንነሳ ችግሮቹ እንደነበሩ ሆነው እንዲያውም በቂ እንቅልፍ ያለማግኘት ችግር ተወምሮበቸው እናገኛቸዋለን፣ በዚህም ጊዜ ህይወታችን ይታወክል።

ወገኖች ከዚህ ዓይነት ችግር ለመውጣት የምንችለው በዛሬው ዕለት እኛነታችንን ተቀብለን ለለእኛነታችን ጌታን ተመስገን ስንለው ነው። እንግዲህ ለለሁሉ ነገር የለጠንን እግዚአብሔርን እናመስግን። እግዚአብሔር ያደረገንን ሰው እንሁን እንጂ ሌሳውን ለመምሰል በምኞት እንዳንሰቃይ እግዚአብሔር ይርዳን።

ጸ ሎ ት
እኔነቴን በራሴ ሃይል ለመለወጥ ከመታገል እርዳኝ።



የንባብ ክፍል ዘፍ 28፡18 22

## ከእግዚአብሔር ጋር የምንኖረው ኑሮ

«እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ቢሆን እግዚአብሔር አምላኬ ይሆንልኛል» ዘፍ 28፡20 21

ከእግዚአብሔር ጋር በምናደርገው ጉዞ በጣም ደስ የሚያሰኘን ትልቁ ነገር በሕይወታችን የሚሠራው ታላቅ ሥራ ነው። በተለይም ሕይወት እንደ ከርታ ተበውዘብን፣ መቺጠሪያው ውሉ ጠፍቶብን፣ አንዳንዴ በውን ይሁን በቅዠት እንዴት እንደምንኖር ማወቅ ሲሳነን ከእግዚአብሔር ጋር መገናኘት የጠለቀ ሰሳምንና እርከታን ይሰጣል። እግዚአብሔር ከሕይወታችን የማይጠፋ ማህተም መተው ሲፈልግ ብዙ ጊዜ ሰዎችን በእንዲህ ዓይነት ወቅት ይገናኛቸዋል። ያዕቆብን በእንዲህ ዓይነት ጊዜ ነው የተገናኘው። ያዕቆብ ከኒሳ የተወው

1) በዕድሜው የገፋ እባት። በመከከለኛው ምስራቅ የልጆች በተለይም የወንድ ልጆች ትልቅ ኃላፊነት በዕድሜ የገፉ ወሳጆቻቸውን እንደሚገባ ጦሪው መቅበር ነው። ይስሀቅ «እነሆ እረጅሁ የምሞትበትንም ሰዓት አሳውቅም» በሚልበት ወቅት ነበር ዋሉት የሄደው።

2) ግራ የተጋባች እናት ነበረችው። መንታ ልጆቿ ኤሳውና ያዕቆብ በማህፀኗ ከተፀነሱበት ጊዜ ጀምሮ በውስጧ የተፈጠረ ጥያቄ ያልተመሰሰለት። የሚጣሉ ልጆች በዕድሜው የገፋ ባል የነበራት የነፍሷን ሃዘን የምታጫውተው የልብ ሰው የሌሳት ሌት ነበረች።

3) መራራ የሆነ የሚጠሳውና የሚያሳድደው ወንድም። የጠሳትን ጠብና ጥሳቻ ለመረዳትና እራሳችንንም ለመከሳከል መዘጋጀት ይቻላል። ወንድም ግን ጠሳት ሲሆን ከባድ ነው። ብትመቱት አያምርም፣ ለሰው ብታወሩት አያምርም፣ ለለዚህ ያዕቆብ ለነፍሱ ፈርቶ ሸሸ።

4) ከልጅነት እስከ አርባ ዓመት ድረስ ያደገበትን ሃገር ትቶ ነበር። እግዚአብሔር በተገለጠለት ወቅት ተምሮ የያዘው ዲግሪ ወይም ሰርቶ ያጠራቀመው ሃብት አልነበረውም። ብቸኛ ሰሰ የአብርሃም አምላክ የአባቱም የይስሃቅ አምላክ ተገለጠለት። በሃብትና በዘር እንደሚባርከውም ቃል ኪዳን ገባለት። የሚያናግረው እንዳች በሌለበት ጊዜ አያቱንና አባቱን ራሱንም ጭምር ደህና እድርጎ የሚያውቅ ሕያው አምላክ ያዕቆብን አነጋገረው። የሚያገባትን ሚስት ሳያውቅ ዘሩ እንደባህር አሸዋ እንደሚበዛ ተስፋ ገባለት። በስደት ሳይ እያለ በሃብት እንደሚባረክ ነገረው። የያዕቆብን አምላክ አምላክችን ብናደርገው በእንዲህ ዓይነት በረከት መባረክ እንችላለን።

ጸ ሎ ት የአብርሃም የይስሐቅ የያዕቆብ አምላክ ሆይ ለእኔም የግሌ አምላክ ሁን።

የንባብ ክፍል ዘፀ 14 10 31

## ማሰናከያ ወይስ መሸጋገሪያ

«እግዚአብሔርን ለሚወዱ እንደ ሃሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን።» ሮሜ 8 28

ሕይወት ደስ በሚያሰኙና ደስ በማያሰኙ ነገሮች የተሞላ የሚመስልበት ጊዜ አለ። በኑሮ ችግር ሲገጥመን ወደፊት የምንገፋውን ጉዞ ሊያሰናክልብን፣ ቢሆን ወደኋላ ሊመልሰን ባይሆን ደግሞ ወደፊት እንዳንጓዝ ሊያቆመን ነው ብለን እናስባለን። ስለዚህም ማንም ሰው መቸገርን አይወድም። ሆኖም በመጽሃፍ ቅዱሳችን ውስጥ ቅዱሳን ችግር የማሰናከያ ድንጋይ ሳይሆን በጌታ የመሸጋገሪያ ድንጋይ ሆኖላቸው እናያለን።

እስራኤላውያን ከግብጽ ወጥተው ቀይባህር ሲደርሱ በሰው ዓይን ትልቅ ችግር ደርሰባቸው ነበር። ከፊታቸው ቀይ ባህር፣ በኋላቸው የፈርዖን ሠራዊት ነበር። ህዝቡም በሙሴ ላይ አንጎራጎሩ፣ ወደ እግዚአብሔርም ጮኹ። ይህ ችግር ለጉዞአቸው ማሰናከያ ቢመስልም የእግዚአብሔርን እጅ እንዲያዩ፣ የመሸጋገሪያም ድንጋይ ሆናቸው። እግዚአብሔር ባህሩን ከፍሎ በደረቅ መሬት አሰለፋቸው።

ማርያምና ማርታ ወንድማቸው አልዓዛር በታመመ ጊዜ መልዕክተኛን ወደ ኢየሱስ ላኩ። ኢየሱስ በቢታንያ ቢኖር ለወንድማቸው ፈውስ እንደሚኖር ያውቁ ነበር። ሆኖም ኢየሱስ በዘገየ ጊዜ አልዓዛርም ሞተ፣ ተስፋቸውም ከወንድማቸው ጋር ተቀበረ። ተስፋ ያደረጉት ኢየሱስ በመጣ ጊዜ ግን ለተስፋቸውና ለወንድማቸው ፈውስ ላይሆን ትንሳኤን ሰጣቸው። በሽታም ሆነ ሞት ለዚህ ቤተሰብ የማሰናከያ ድንጋይ አልሆነም። ይልቁኑ የእግዚአብሔርን እጅ የሚያዩበት የመሸጋገሪያ ድንጋይ ሆነ።

አዎ መጽሃፍ እንደሚል እግዚአብሔርን ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት እንዳንድ ነገሮች ላየሆኑ ነገር ሁሉ ለበጎ ነው። ወገኔ ዛሬም በፊትህ የቆመ ችግር በእግዚአብሔር ሃይል የማሰናከያ ድንጋይ ላይሆን የመሸጋገሪያ ድንጋይ ይሆንልሃልና በእርሱ ታመን።

ጸ ሎ ት

በማየት ላይሆን በእምነት እንድመላለስ እርዳኝ።



የንባብ ክፍል ማቴ 6 25 33

## እግዚአብሔርን መፍራት

« እግዚአብሔርን መፍራት የሕይወት ምንጭ ነው »(ምሳሌ 14 27)

በዓለም ላይ በሰዎች ሕይወት ውስጥ የሚኖር ሁለት ዓይነት ፍርሃት ሲኖር እንደኛው ወደጭንቀት፣ ወደግራ መገባት፣ መረበሽ ከዚያም ሲበዛና ሲጠነክር ወደሞት ጎዳና የሚወስድ ፍርሃት ሲሆን በዚህ ፍርሃት ሥር ያሉ ስለሞት፣ ስለወደፊት ኑሮ ስለብዙ ነገሮች በመጠነቅ የሕይወትን እርካታና ደስታ ያጡ ይሆናሉ።

ሁለተኛው ፍርሃት ግን ወደ ሕይወት፣ ወደ ቅድስና ወደ ደስታና ሰላም ከሁሉም በላይ እግዚአብሔርን ወደ ማወቅና ማክበር የሚመራ የነጻነት ሕይወት ነው።

አንባቢ ሆይ በየትኛው የፍርሃት ክፍል ውስጥ እንደምትመደብ አንተ ታውቃለህ። ዛሬ እግዚአብሔርን ከለመፍራት የተነሣ ሰዎች በሚያደርጉት ነገር ጋላፊነት እየጎደላቸው በኃጢአት፣ በዓለማዊነት በመጠላለፍ በሚያሳዝን ጎዳና ይጓዛሉ።

ስለዚህ ኑሮአችን፣ ሕይወታችን፣ ንግግራችን የምናልመው ዓላማ፣ የምናቅደው እቅድ፣ ዓምልኮአችንና አገልግሎታችን እግዚአብሔርን በመፍራት በማክበር ሊመሠረት ይገባል።

« ቀኑን ሙሉ እግዚአብሔርን በመፍራት ኑር በእውነት ፍጻሜ አለህና ተስፋህም አይጠፋምና» (ምሳሌ 23 17) የሚለውን ቃል በመታዘዝ እንኑር።

ጸ ሎ ት

አቤቱ አባት ሆይ አንተን በመፍራት ልኑር የሕይወቴ አከሄድ እንዲያምር። አሜን!

የንባብ ክፍል ዮሐ 14 25 31

## ሰ ላ ም

አብዛኛውን ጊዜ ሰላም የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የሚውለው ውጫዊ ግጭት መወገዱን ለማመልከት ነው። ውጫዊ ችግር ምናልባት የፖሊስ አርምጃ ወይም የፍርድ ቤት ብያኔ ያስወግደውና በቦታው ፀጥታ ተተክቶ ሰላም ሆነ ሊባል ይችላል። ነገር ግን ቀኑ ሊመሽ እንቅስቃሴ ሁሉ ቆሞ፡ ነገር ሁሉ ረጭ ባለበት ጊዜ በብዙ ሰዎች ሕይወት ውስጥ ከፍተኛ ግጭት ይከሄዳል። ይህ ግጭት ውስጣዊ ስለሆነ የፖሊስም አርምጃ ሆነ የፍርድ ቤት ውሳኔ ሊፈታው አይችልም። ነገር ግን የውጫዊም ሆነ የውስጣዊ ሰላም አለታ የሆነው ኢየሱስ ሰላም ለአንተ ይሁን ሊል ግንኛውም ዓይነት ግጭት ይቆምና ሁሉ ነገር ሕብረትና ሰምንነት ያለው ይሆናል።

ለሰው ውስጣዊ ግጭት መነሻው ሰው የጽድቅን ፈተና የወደቀ ሆኖ ሳለ፡ የወደቀ መሆኑን ባለመቀበል ጻድቅ ለመሆን በሚያደርገው ጥረትና መቸም ጻድቅ ለመሆን ባለመቻሉ መከከል ያለ ችግር ነው። ከዚህም ቅራኔ የተነሣ ሰው ሊያደርጋቸው ወይም ሊያገኛቸው በሚፈልጋቸው ነገሮች ፍጹምነትን አያገኝም። ስለዚህ እያንዳንዱ ቀን ለሰው የውስጣዊ ጦርነት ቀን ነው። ሰው ግን በራሱ ሊጸድቅ አለመቻሉን አውቆ በክርስቶስ ኢየሱስ የተሰጠውን ጽድቅ ቢቀበል ለችግሩ ሁሉ መፍትሄ ያገኛል፡ ውጤቱም ውስጣዊ ሰምንነት ይሆናል።

ወገኔ አንተስ እያንዳንዱን ቀን በጌታ ሰላም ውስጥ ሆነህ ታሳልፈዋለህ ወይስ ከላይ በተገለጸው ሁከት ውስጥ? በሁከት ውስጥ ከሆነ የሰላምን አለታ ኢየሱስን የህይወትህ አለታ በማድረግ አንተም በዚህ ሰላም ልትረከብ ትችላለህ።

ጸ ሎ ት የሰላም አለታ ሆይ የህይወቴም አለታ ሁን።



የንባብ ክፍል ኤር 17 5 9

## ታላቁ ሐኪም

«የሰው ልብ ከሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ እጅግም ከፉ ነው፡ ማንስ ያውቀዋል?» (ኤር 17 9)

ቶሮንቶ በተባለው የካናዳ ከተማ አንዲት የእንግሊዝኛ ቋንቋ መናገር የማትችል የአረብ አገር ተወላጅ በጠና ታማ ድንገተኛ ክፍል ከተወሰደች በኋላ አብዝታ በመጨህና ፀጉሯን በመንጨት ሐኪሞቹንና ነርሶቹን አስቸገረች። በሽታዋን እንዳትናገር ቋንቋ አታውቅ፡ አስተርጊሚ የሰ፡ ውሽት ብቻ ሆነ። በዕለቱ ተረኛ የነበረው ዶክተር መጠነኛ ምርመራ ከደረገ በኋላ በሽታዋ የአዕምሮ እንጂ የአከል አይደለም ብሎ እንደደመደመ በሽታዋ ፀንቶ አረፈች። ሬሳው ሲመረመር ለክስ የከንሰር በሽታ ጉበቷን አጥቅቶ ኖሯል የሞተችው። የተሳሳተ ምርመራ አድርጎ ያለናበታት ዶክተር ይህን ሰምቶ እጅግ እንደተፀፀተ የከተማይቱ ጋዜጣ አስፍሯል።

መንፈሳዊ ችግር ያለባቸው አንዳንድ ሰዎችም የተሳሳተ ምርመራና መፍትሄ እንደሚሰጣቸው ከውጤቱ መረዳት እንችላለን። አንዳንዶች በኃጢአታቸው ምክንያት የጎሊና ወቀሳ ይዟቸው ይለቃያሉ። መልከም ያደረጉ የሚመስላቸው መንፈሳዊ ምክር ሰጋሽች ለበሽታው ጊዜያዊ እፎይታ የሚሰጥ መፍትሄ ሊሰጡ እናያለን። አንዳንዶች ከተማ እንዲቀይሩ፡ ሌሎች ቤት እንዲለውጡ ከፊሎች ደግሞ ትዳራቸውን እንዲተው ይመከራሉ። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ጥልቅ የመንፈሳዊ ሕይወት ችግር ያለባቸው ሰዎች በስህተት «የአዕምሮ ሞንቀት ነው» በማለት ወደማይፈለግ ዓይነት ሐኪም ቤት ይላክሱ።

እኛ ክርስቲያኖች በኃጢአት የተቸገረ ሰው ስናገኝ ወዲያውኑ ለመንፈሳዊ ህይወቱ መፍትሔ ወደሆነው ወደ ኢየሱስ መምራት አለብን። እርሱ የልብን ውሽት ለምቶ የኃጢአትን በሽታ በአንድ አፍታ መፈወስ የሚችል ታላቅ ሐኪም ነው።

ዛሬ የአግዚአብሔር መንፈስ ለዎች ኃጢአታቸውን ተገንዝበው ወደ ፈዋሹ ወደ ኢየሱስ እንዲመጡ ዓላማው ለለሆነ ምህረትን ሊቀበሉ ወደሚችሉበት ወደ ኢየሱስ አንምራቸው።

ጸ ሎ ት
አምላኬ ሆይ ፈዋሽነትህን ለለየሁ ሌሎችን ወደአንተ እንድመራ እርዳኝ።

**የንባብ ክፍል** (2ኛ ጢሞ 4 1 8)

## የጽድቅ አክሊል

«ሩጫውን ጨርሻለሁ ወደፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል» 2ጢሞ 4 7 8

በአገራችንም ሆነ በዓለም ዙሪያ በሩጫ ውድድር ተደናቂነትን ያተረፈው የመቶ አለቃ አበበ ቢቂላ አንድ ጊዜ ተከቦ በደረገው የማራቶን ውድድር ላይ ያደረገው ሯጣ ለሩጫ ስለልተስማማው ሩጫውን አቋርጦ ሯጣውን ከወለቀ በኋላ ውድድሩን በባዶ እግሩ ቀጠለ። ተመልከቾች በነገሩ ተደንቀው «እግሩን ስለሚያመው ውድድሩን አቋርጦ ይወጣል» ብለው ገምተው ነበር። ይሁን እንጂ አበበ ቢቂላ ከሌሎች ተወዳዳሪዎች ሁሉ ቀድሞ በመግበት የዋንጫው ባለቤት መሆኑን አረጋገጠ። በባዶ እግር በመሮጥ አሸናፊ በመሆኑ እስከዛሬ ድረስ ስሙ በስፖርት ሚዳዎች በጀግንነቱ ዘወትር ይወሣል።

ሐዋርያው ጳውሎስ የምድር ላይ ዘመኑ ፍጻሜ እንደተቃረበ በመገንዘቡ «ሩጫውን ጨርሻለሁ» ብሎ ይደነግጋል። እግዚአብሔር እንዲሠራ የሰጠውን ሥራ ጨርሷል። በመከራ ውስጥ ሊያልፍ ታከቶ ወይም ደከመኝ ብሎ ሥራውን አላቋረጠም። በታማኝነት በማዕበል ቢያልፍ፣ እሥር ቤት ቢሰቃይ፣ ቢገረፍ፣ «በቃኝ» ያለበት ጊዜ ባለመኖሩ ዛሬ የአዲስ ኪዳን የዕምነት ጀግና በመባል ይታወቃል። እግዚአብሔር በዚህ በጎ ሠራተኛ የጽድቅ አክሊል እንደተዘጋጀለት መገንዘብ እንችላለን።

የክርስትናን ሕይወት ስንኖር ለኑሮው የማይስማሙ አጉል ሚማዎች ያጋጥሙን ይሆናል። እንደምሣሌ ለመጥቀስ፣ ቅዱስ ውሸት መዋሸት፣ አንዱ ነው። እንደዚህ ያሉ ጥቃቅን ኃጢአቶች የክርስትናን ሩጫ በሚገባ እንዳንሮጥ ይከለክሉናል። በድፍረትም «ሩጫውን ጨርሻለሁ» ማለት አንችልም። ይህንኑ በማሰብ ነው ሐዋርያው «ሸክምን ሁሉ ቶሎም የሚከበንን ኃጢአት አስወግደን የዕምነታችንንም ራስና ፈጻሚውን ኢየሱስን ተመልከተን በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንሩጥ» ብሎ የሚመክረን።(ዕብ 12 2)

የሩጫው ተከፋይ የሆንክ ክርስቲያን ወገኔ እንግዲያው አሸናፊ ሆነህ የጽድቅ አክሊል ባለቤት መሆን እንድትችል የሚከብድህን ኃጢአት ቶሎ አስወግድ። እርሱ ከኃጢአታችን ሊያነፃን የታመነና ጻድቅ ነው።

ጸ ሎ ት

ጌታ ሆይ ሩጫውን ጨርሼ የድል አክሊል ባለቤት እንድሆን አብቃኝ።



**የንባብ ክፍል** ዮሐ 21 1 14

## የሚያስፈልገኝን ያውቃል

«ኢየሱስም ልጆች ሆይ እንዳች የሚበላ አላችሁን? አላቸው።» ዮሐ 21 5

አንድ አረብ በበረሃ ውስጥ ውሃን የሚያጠጣው ሰው እንዲገናኝ ተስፋ እያደረገ ሲጓዝ ከግመል መሚኛ የወደቀ የተጠቀለለ ዕቃ አገኘ። ይህም ሰው በደስታ ምናልበት እዚህ ውስጥ ውሃን የያዘ ዕቃ ይገኛል በማለት በጥድፊያ ከፈተው ነገር ግን ያገኘው ዕቃ ውሃ ላይሆን ዋጋው እጅግ የከበረ አልማዝና ወርቅ ነበር። ይህም ሰው ከጥማት የሚያረከው ውሃ እንዳልሆነ በተረዳ ጊዜ በንዴት ያንን የከበረ አልማዝና ወርቅ ወርውሮ ጣለው።

ሰው በችግሩ ሰዓት የደረሰለትን እንዲሁም የተደረገለትን ውለታ አይረሳም። ያንንም ውለታ ከተደረገለት ሰው በላይ አብልጦ የሚረዳ የለም። ጌታ ኢየሱስ ከትንሣኤ በኋላ ለደቀ መዘሙርቱ ለሦስተኛ ጊዜ የተገለጠላቸው በጥብርያዶስ ባህር አጠገብ ነበር። ደቀ መዘሙርቱ ሌሊቱን በሙሉ ዓሳ ለማጥመድ ደክመው እንዳችም ላያገኙ ተርበው ነበር። ጌታ ኢየሱስም «እንዳች የሚበላ አላችሁን?» በማለት ንግግር ሲጀምር እንመለከታለን። ደቀመዘሙርቱም የሚበላ እንደሌላቸው በመለሱለት ጊዜ «መረቡን በታንኳይቱ በስተቀኝ ጣሉት ታገኙማላችሁ» አላቸው።

በሌላም ሥፍራ ደቀ መዘሙርቱ ተሰብስበው፣ አይሁድንም ስለፈሩ ደጆቻቸውን ዘግተው በፍርሃት ሳሉ፣ አሁንም ጌታ ኢየሱስ በመካከላቸው ቆሞ «ሰላም ለእናንተ ይሁን» ሲል እንመለከታለን። የእኛ ጌታ ለተራበው ምግብን፣ ለፈራውም ሰላምን መስጠት ያውቅበታል። እርሱ የሚያስፈልገንን ያውቃል። እንደ መልካም አረኛም ዘወትር ወደ ለመለመ መስክ ወደ ዕረፍትም ውሃ ይመራናል።

ዛሬ ለአንተ የሚያስፈልግህ ምን ይሆን? የልብህን ጥማት ታዳጊህ ያያል። «በነጋም ጊዜ» ለደቀ መዘሙርቱ የተገለጠው ኢየሱስ ለእንተም ይደርሳል። መዝሙረኛው ዳዊት እንዳለው «ልቅሶ ወደማታ ይመጣል ጥዋት ግን ደስታ ነው።» መዝ(30) 5 ወገኔ ሆይ ደስ ይበልህ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነው።

ጸ ሎ ት

የሚያስፈልገኝን ታውቃለህና አንተን መድሃኒቴን እጠብቃለሁ።

የንባብ ክፍል ኢሣ 40 12 31

## በማን ትመስሉታላችሁ

«እንግዲህ እግዚአብሔርን በማን ትመስሉታላችሁ? » (ኢሣ 40 18)

በዚህ ምድር ላይ የምንኖረው ኑሮ እንዳንድ ጊዜ በአውሮፕላን ላይ ከሚበሩ ተሣፋሪዎች ጋር ይመሣሰላል፡ ከጥቂት ደቂቃ በኋላ ከሚፈጸም ምንም ዓይነት እደጋ ለማምለጥ ዋስትና የለንም።

ትኩር ብሎ ለተመለከተ ሰው የአውሮፕላን ተሣፋሪዎች ብዙዎቹ ሲያንቀላፉ፡ እንዳንዶች መጽሐፍ ያነባሉ። ከፊሉ ካርታ ሲጫወት ሌላው ሞቅ ያለ ወግ ያወጋል። ድንገት አውሮፕላኑ ወድቆ ቢከሰከስ ተሣፋሪዎቹ ከሞት የሚያመልጡበት ምንም ዓይነት ዋስትና የላቸውም።

የለው ልጅም በዚህ ምድር ላይ ለመኖሩ ምንም ዋስትና የለውም። ታላላቅ መንግሥታት አለኝታችን ብለው የጠበጡትን ቦምብ ቢጥሉ በአንድአፍታ ዓለምን እንዳልነበረች ያደርጊታል። የምድር መናወጥ፡ የውሃ መጥለቅለቅ የኢኮኖሚ መዘበትና የጦርነቶች መነሣት የዚህን ዓለም ሕዝብ እንቅልፍ ከሚነሱት ሁኔታዎች ጥቂቶቹ ናቸው።

ክርስቲያን ከሚመጣው ቁጣ በደሙ የተከለለ ነው። ከሁሉ በላይ ግን የሚደነፈውና የሚታመነው እምላክ ፍጥረታት ሥርዓታቸውን ተከትለው እንዲሄዱ የሚያደርግ ታላቅ ንጉሥ መሆኑን ስለሚያውቅ በሚፈጠሩት ሁኔታዎች አይብረከረክም። የእግዚአብሔር ቃል እንደሚያረጋግጥልን የዚህ ዓለም ውሆች (ውቅያኖሶች ፡ ሐይቆችና ወንዞች ሁሉ ተደምረው) በእምላካችን እፍኝ ላይ እንዳለች ጠብታ ናቸው። ስለዚህ በአየር ላይ እንብረር፡ በምድር ላይ እንሁን ከምድር በታች ሊያስፈራን የሚችል እንዳች ሊኖር አይገባም።

ወገኔ ዛሬ የሚያስፈራራህ ነገር ይኖር ይሆን? ምድራችን ሲያበቃላት ምን ይውጠኛል? ልጆቼስ፡ ቤቴስ ንብረቴስ ትል ይሆን? ሆድህ አይባባ፡ ድፍረትህ በጌታ ላይ ይሁን። እርሱ ሁሉን ይቆጣጠራልና።

ጸ ሎ ት
እቤቱ በእንተ ላይ አብዝቼ እንዳርፍ ለሳሜን አብዛ!



የንባብ ክፍል 2ኛ ቆሮ 4፡1 18

## አ ን ታ ከ ት ም

«ስለዚህ ምክንያት ምህረት እንደተሰጠን መጠን ይህ አገልግሎት ሰላለን እንታክትም»። ቁጥር 1

ሐዋርያው እደራ የተሰጠውን የሰብከት አገልግሎት በሰላም እንዲፈጽም ዕድል በይለጠውም በመገፋት በማመንታት በመሰደድ በመውደቅ ተልእኮውን መፈጸም እንዳለበት ያብራራል። እዎን ሐዋርያው ጳውሎስ ምንም እንኳ መከራ ቢደርስበት በደረሰበት መከራ እዝኖ አገልግሎቱን ከመፈጸም አላቋረጠም። ሐዋርያው የደረሰበትን መከራ ለመታገስ የቻለበት ምክንያት ጊዜያዊና ምድራዊ ሥቃይ በዘልዓለማዊ ሰማያዊ ደስታ እንደሚለወጥ ስላወቀ ነው። ስለዚህም ነው በተለያየ ቁጥር የድል መዝሙር የሚዘምረው።

ድል ነሺው ሐዋርያ በሁሉ እንገፋለን እንጂ እንጨነቅም እናመነታለን እንጂ ተስፋ እንቆርጥም እንለደዳለን እንጂ አንጣልም እንወድቃለን እንጂ እንጠፋም እያለ ይዘምራል። ጳውሎስ ከሞት በሻገር ሕይወት እንዳለ ያወቀና የተረዳ ሐዋርያ ነው። ስለዚህም ነው የኢየሱስ ሕይወት ደግሞ በሥጋችን ይገለጥ ዘንድ ሁልጊዜ የኢየሱስን መሞት ተሸክመን እንዘራለን የሚለው። እዎን እኛም ዛሬ በሚገጥሙን መከራዎችና ፈተናዎች የድል መዝሙር እየዘመርን ለመጊዝ የምንችለው የሚታየውን ዋላል የሆነ የጊዜው መከራችን ሳይሆን የማይታየውንና ዘለዓለማዊውን ተስፋ ስናደርግ ነው። እንሮጣለን እንደክምም፡ እንሄዳለን እንዝልም፡ ጌታ ኃይላችን ነው እንወድቅም።

ጸ ሎ ት ጌታ ሆይ ከመታከት ጠብቀኝ

የንበብ ክፍል 2ኛ ቆሮ 6 1 10

## የመዳን ቀን አሁን ነው

«በተወደደ ሰዓት ሰማሁህ በመዳንም ቀን ረዳሁህ ይላልና፡ እነሆ የተወደደ ሰዓት አሁን ነው፡ እነሆ የመዳን ቀን አሁን ነው።» 2ኛ ቆሮ 6 2

አንዳንድ ሰዎች ከምግብ በስተቀር ለሁሉ ነገር ነገ ማለት ይቀለቸዋል። አንድ ጊዜ የሁለተኛ ደረጃ ክርስቲያን ተማሪዎች ጎብረት ለምስክርነት ወጥተው ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት ሲናገሩ ለሚዎቹ የሚሉትን ሁሉ በጥሞና ከደመጡ በኋላ «አሁን ጌታን ተቀበል» ተብለው ሲጠየቁ አይ እኔ ገና ወጣት ነኝ፡ ብዙ መልከም ዕድል ከፊቴ ይቆየኛል፡ በይሆን እድሜዩ ሃምሳ ወይም ስድሳ ሲሆን እቀበለዋለሁ» የሚል መልስ ይሰጢቸው እንደነበር ይናገራሉ።

የወንጌልን ድምጽ ሰምተው ለሚቀበሉና ቸል ለማይሉ ቃሉን በሰሙ ቁጥር ያቀን የተወደደ ቀንና የመዳን ቀን እንደሆነ የእግዚአብሔር ቃል ይናገራል። ይሁን እንጂ የተወደደውንና የመዳኑን ቀን ልብን በማደንደንና በማጠንከር ከለፈ ሲመጣ ከለው ከእግዚአብሔር ቁጣ ለማምለጥ አይቻልም። ስለዚህም ነው ሐዋርያው በተወደደ ሰዓት ሰማሁህ በመዳንም ቀን ረዳሁህ እነሆ የመዳን ቀን አሁን ነው፡ እነሆ የተወደደ ሰዓት አሁን ነው እያለ የሚያስጠነቅቀው።

ማናችንም ብንሆን ነገ የሚሆነውን ነገር ለማወቅ ምንም ዓይነት ችሎታ የለንም። የምንኖረው በተስፋ እንጂ ነገ ወይም ከአንድ ሰዓት በኋላ በሕይወታችን ለሚፈጸም ነገር ምንም ዓይነት ዋስትና የለንም። ለዚህ ነው መጽሐፍ ቅዱስ የመዳን ቀን አሁን ነው የሚለው።

ወገኔ ወንጌልን ስንት ጊዜ ሰምተሃል? ስንት ጊዜስ ነገ ጌታን እከተለዋለሁ በማለት የጥሪውን ቃል ችላ ብለሃል? ስንት ጊዜስ ነገ ጌታን እከተለዋለሁ በማለት የጥሪውን ቃል ችላ ብለሃል? ይህ ዘመን የእግዚአብሔር የምህረት ዘመን ነው። ለሁሉ ጊዜ አለው ብሎ ንጉሥ ሰሎሞን እንዳወጀ ለፍርድም ጊዜ አለውና ያ የፍርድ ዕለት ሳይደርስ ፈጣሪህን አሁን አስበው። የመዳን ቀን አሁን ነውና!

ጸ ሎ ት
ጌታ ሆይ ልቤን ለወንጌልህ ጥሪ ከፈትልኝ።



የንበብ ክፍል ሉቃስ 15 3 32

## የጠፋው በግ

«ተነስቼም ወደ አባቴ እሄዳለሁና ተነስቶም ወደ አባቱ መጣ።» ሉቃስ 15 18

እግዚአብሔር ከሚታወቅባቸው ባህርያቶቹ አንዱ የምህረት አምላክ መሆኑ ነው። በእውነተኛ ልብ በንሥሃ ወደ እርሱ የሚመለሱትን ሁሉ እጁን ዘርግቶ በምህረት ይቀበላል። እውነተኛ ንሥሃ እግዚአብሔርን ብቻ ሳይሆን መላዕክቶቹንም ደስ ያሰኛል።

በዛሬው የንበብ ክፍላችን የጠፋውን ኂላም የተገኘውን የዚህን ታናሽ ልጅ ታሪክ እንመለከታለን። ይህ ልጅ ከአባቱ ድርሻውን ወስዶ ወደ ሩቅ አገር እንደሄደ እናያለን። በዚያም ገንዘቡን ሁሉ ካባከነና ከበተነ በኋላ በዚያች አገር ጽኑ ራብ ሆነ። ይህም ሰው አሪያዎች ከሚበሉት አሰር ሲጠግብ ይመኝ ነበር፡ የሚሰጠውም አልነበረም። አባከኑ ልጅ ግን ወደ ልቡ ተመለሰ። «ተነስቼም ወደ አባቴ ቤት እሄዳለሁ» አለ። በዚህም ብቻ አላበቃም ግን «ተነስቶም ወደ አባቱ መጣ።»መጽሃፍ ቅዱሳችንም «አርሱም ገና ሩቅ ሳለ አባቱ አየውና አዘነለት፡ ሮጦም አንገቱን አቀፈውና ሳመው» ይለናል። በዚህም ብቻ አላበቃም ግን የለበውን ፈሪዳ አረደለት፡ በዚያም ቤት ደስታ ሆነ።

ወገኔ ዛሬ ከጌታ ቤት ርቀህ ህይወትህ በረሃብና በጥማት ትቃጠል ይሆን? ይህንን ረሃብ ማርከት የምትችለው እንደዚህ ልጅ ወደ ልብህ ተመልሰህ «ወደአባቴ ቤት እመለሳለሁ» ስትልና እንደዚህ አባከኝ ልጅ ወደ አባትህ ወደ እግዚአብሔር ቤት ስትመለስ ነው የጠፋው ልጅ አሪያዎች ከሚበሉት አሰር ሲጠግብ ይመኝ ነበር፡ ወደ አባቱ ቤት በተመለሰ ጊዜ ግን ረሃቡን በአባቱ ፍቅር፡ በለበውም ፈሪዳ አጠገበ። ዛሬም የእግዚአብሔር አባትህ የምህረት እጅ ለአንተ ተዘርግቷል። ልብህን ከመንገድህ ጋር ወደ እግዚአብሔር መልስ እርሱም ይቀበልሃል።

ጸ ሎ ት
አባት ሆይ ወደ ልቤ እመለስ ዘንድ የተዘረጉትንም የፍቅር እጆችህን አይ ዘንድ እርዳኝ።

የንበብ ክፍል ኢሣ 9 6 7

## ል ደ ት

«እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ።»ማቴ 1 21

በዚህ ዘመን በተለይም በሰሜን አሜሪካ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል የተሰላተ ትርጉም ተሰጥቶት እንመለከታለን። ለዎች ስጦታ የመለዋወጫና በተለያየ የንግድ ዘርፍ ለተሰማሩ ደግሞ ጥሩ የማትረፊያ ጊዜ አድርገው ሲቆጥሩት እንመለከታለን። ይህ ጊዜ ለነጋዴዎች ማትረፊያ ሳይሆን ለሰው ዘር በሙሉ የሀይወት ማትረፊያ የሆነው ጌታ ኢየሱስ የሚነገርበተና የሚታወጅበት መሆኝ አለበት። እርሱን በማመን ሰው ከዘላለም ሞት ይተርፋል፡ እርሱን በማመን ሰው ከበሽታ ይተርፋል፡ እርሱን በመመን ሰው ከሃዘንና ከስቃይ ይተርፋል፡ አዎ እርሱን በማመን ሰው ጠላት ዲያብሎስ ከዘጋጀለት መራራ ድግስ ይተርፋል።

ለእኛ ለአማኞች ይህ ቀን በአመት አንድ ጊዜ የምናከብረው መሆን የለበትም። ለእኛ እያንደንዱ ቀን የልደት ቀን ነው። ይህንን መድሃኒት የሆነ ጌታ ለሰዎች በነገርንና በስተዋወቅን ቁጥር፡ እሺ ብሎም ልቡን በሚከፍት ሰው ውስጥ ልደት ይሆናል። እውነተኛው የልደት ቀን ሰዎች ጌታ ኢየሱስን እንደ አዳኛቸው ሲቀበሉና ሲወሰኑ ነው።

እንግዲህ ዛሬም ሆነ ከዚህ በኋላ በምንኖርበቸው ቀናት ሰውን ለአንዲና ለዘላለም ሲቀይር የሚችለውን፡ የአንድ ቀን ሳይሆን የዘላለም ደስታን የሚሰጠውን ይህን ኢየሱስን ለሌሎች እንንገር። ያኔ ሰዎች ህይወታቸውን ያተርፋሉ፡ እውነተኛ ልደትም በልባቸው ይሆናል። ይህንንም ልደት እኛ ብቻ ሳንሆን የእግዚአብሔርም መላእክት በሰማይ ያከብሩታል። ጌታ ኢየሱስ በሥጋ ሲወለድ የዘመሩለት መላእክት ዛሬም በሰው ልብ ውስጥ ሲወለድ በሰማይ ደስ ይላቸዋል።

ጸ ሎ ት ጌታ ሆይ የልደት ቀንህን አንተ ማን እንደሆንክ እንድመለክርበት እርዳኝ።



የንበብ ክፍል «እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ።» ማቴ 5 14

## የዓለም ብርሃን

ጌታ ኢየሱስ በታወቀው የተራራው ሰይ ስብከቱ ሲከተሉት ለነበሩት «እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ» ብሎ ሲያስተምር እንመለከታለን። በዚሁም ክፍል ሳይ « ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ ይላቸዋል።»

ዉለማ በይናር ብርሃን በላስፈለገ ነበር። በፍጥረት መጀመሪያ «ምድርም በዶ ነበረች አንዳችም አልነበረበትም ዉለማም በጥልቁ ላይ ነበረ የእግዚአብሔርም መንፈስ በውሃ ላይ ሰፍፎ ነበር። እግዚአብሔርም ብርሃን ይሁን አለ፡ ብርሃንም ሆነ» በማለት መጽሃፍ ቅዱሳችን ይነግረናል። እግዚአብሔር በመጀመሪያው ቀን ብርሃንን የፈጠረው ዉለማን ለማሸነፍ ነበር። ጌታ ኢየሱስም ተከታዮቹን «እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ» ያለው ዓለም በዉለማ ገዝ እጅ ውስጥ ስለሆነች እኛ ይህ እውነተኛ ብርሃን የበራልን ይህንን ብርሃን እያበራን ሰዎችን ከዚህ የዉለማ ግዘት ወደ ብርሃን፡ ይህም ወደ ጌታ ኢየሱስ መንግሥት እንድናመጣ ነው።

በድሮ ዘመን መብራት በዘይት ሃይል እንደሚገኝ መጽሃፍ ቅዱሳችን በተለያዩ ቦታዎች ያሳየናል። በዘፀ 27 20 እግዚአብሔር ሙሴን «አንተም መብራቱን ሁልጊዜ ያበሩ ዘንድ ለመብራት ተወቅጦ የተጠለለ ጥሩ የወይራ ዘይት እንዲያመጡልህ የእስራኤልን ልጆች እዘዛቸው» ብሎ ሲያዘው እንመለከታለን። ይህም ዘይት በብዙ ቦታዎች የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ሆኖ እናየዋለን።

ዛሬም እኛ ጌታ ኢየሱስ በስሙ የጠራን ለዚህ ዉለማ ዓለም እውነተኛ ብርሃን እንድናበራ ነው። ሆኖም ያለ መንፈስ ቅዱስ ዘይት ብርሃናችን ሲበራና ለሰዎች ሲታይ አይችልም። ስለዚህ ጽዋችንን በመንፈስ ቅዱስ ዕለት በዕለት እንዲሞላ መጸለይ አለብን። ለዚህም ነው ጌታ ኢየሱስ «ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ነው» (ዮሐ 6 63) ያለን።

ጸ ሎ ት ጌታ ሆይ ዕለት በዕለት በመንፈስ ቅዱስህ ሙላኝ።

የንባብ ክፍል 2ኛ ቆሮ 1 1 7

## እርሱ ያጽናናናል

«የክርስቶስ ሥቃይ በእኛ ላይ እንደበዛ እንዲሁ መጽናናታችን ደግሞ በክርስቶስ በኩል ይበዛልናልና» ቁ5

በምዕራቡ ዓለም ችግር ያለባቸውን ለዎች ለማማከር ንግድ ቤት ከፍተው የሚሠሩ አያሌ የሥነ አዕምሮ አዋቂዎች ይገኛሉ። እነዚህ ለዎች ችግረኞችን ከችግራቸው እንዴት ነፃ እንደሚወጡ የሚመክሩት እነርሱ ከደረሰባቸው መከራ በመማር ሳይሆን ት/ቤት በጠኑት ጥናት ላይ ተመሥርተው ነው። እንዲህ ዓይነቱ ማጽናናት ከአዕምሮ አንጂ ከልምምድ የሚፈልቅ ስላልሆነ በተመከሪውና በአማካሪው መካከል ጠለቅ ያለ ወዳጅነት አይፈጥርም።

ሐዋርያው መከራና ፈተና ቢደርስበትም በደረሰበት መከራና ፈተና መጠን መጽናናትን ደግሞ በክርስቶስ እንዳገኘ ይገልጻል። ክርስቶስ ስለዓለም ኃጢአት ተገርፎ ተሰቅሎና ሞቶ ብቻ ቢዋር ኖሮ በቅዱሳንና በጻድቃን ላይ የሚደርሱት መከራዎች እጽናኝ ባልተገኘላቸውም ነበር፣ ነገር ግን ክርስቶስ በዚያ ሁሉ መከራ ቢያልፍም የመከራና የፈተና አሸናፊ ሞትን ድል ነሺ ሕያው ሆኖ በአበቱ ዋኝ በክብር ዙፋን ተቀምጧል። ያ ድል ነው ሊሎችን ለማጽናናት ሐዋርያት፣ ቅዱሳንና ለማዕታት ሕይወታቸውን የለውበት። ያም ድል ነው ዘሬ ብዙ አማኝ ክርስቲያኖች የሚጽናኑበት። ሐዋርያው በቃል ብቻ መግለጽ ሳይሆን በሕይወቱ የተለማመደውን ምስክርነት ይገልጻል። ይህ ክፍል ሐዋርያው የተቀበለውን ሥቃይ የሚገልጽ ቢሆንም ከእግዚአብሔር ከፍ ያለ መጽናናትን ለማግኘቱ ደግሞ ራሱ ይመሰክራል። ቅዱሳንና ጻድቃን የሚለቃዩበት ሥቃይ ሁሉ መራራና አሰዛኝ ቢሆንም አስደሳች ውጤት እንደሚፈጥርላቸው ከሕይወታቸው እንረዳለን። እኛም አምላክን በመከራችን ሁሉ ስለሚያጽናናን በመከራ ያሉትን እናጽናና።

ጸ ሎ ት

ጌታ ሆይ ሊሎችን እንዳጽናና በሚደርስብኝ መከራና ፈተና ሁሉ መጽናናትን ስጠኝ።



የንባብ ክፍል ኢዮብ 5 1 27

## ለምስኪኑ ተስፋ አለው

«ሀዘንተኞችን ለደህንነት ከፍ ከፍ ያደርጋል።(ኢዮብ 5 11)

ኢዮብ ስለደረሰበት መከራ መቃተትና ስለ እግዚአብሔር አሠራር መጠየቅ ሲጀምር ከጊደኞቹ አንዱ ቴማናዊው አልፋዝ ስለ እግዚአብሔር አሠራር የሰማውን መናገር ይጀምራል። ይህም በጻድቅና በሰነፍ ለው መከከል ያለውን ልዩነት ነው። ለነፍ ለው ያከማቸው ለሊሳ እንደሚሆንና እንዲሁም እግዚአብሔር ተንከለኞችን እንደሚያውቃቸውና እንደሚይዘቸው አስረድቶ በሊሳ በኩል ደግሞ እግዚአብሔር የሚገስጸው ለው ምስጉን እንደሆነ እግዚአብሔር የሰበረውን የሚጠግን አምላክ እንደሆነ ተግሣፁን መናቅ አስፈሳጊ እንዳይደለ ይናገራል።

የሚገሠፅ ያጠፋ ለው ነው ኤልፋዝም ኢዮብን « አንተ ግን አንዳች ሠርተህ እንደሆነ ለራስህ እወቀው» ቁጥር 27 ይለዋል። ስለዚህም በኤልፋዝ አስተሳሰብ የኢዮብ መከራ ከኃጢአት የመጣ ነው። ግን ነገሩ እንዲህ አልነበረም። ኢዮብ በመከራውም ጊዜ እንኪ አልበደለም። ከዚያ በፊትም ቢሆን ለልጆቹ እንኪ ምናልባት በድለው እንደሆነ በማለት መስዋዕት የሚያቀርብ ለው ነበረ። ልብንና ኩላሊትን የሚመረምር አምላክም ስለ ኢዮብ ጽድቅ ይመሰክራል።

በዚህ ሁሉ ለኢዮብ መጽናናት የሚሆን ነገር አልተገኘም። ግን ኤልፋዝ ከለው ነገር «ለምስኪኑ ተስፋ አለው ክፋት ግን አፍዋን ትዘጋለች» ለተቸገረው ለኢዮብ ተስፋ አለው። የደረሰበት ክፋት ይጠፋል በእርሱ ላይ እስከመጪረሻ አይጨፍርም።

የተቸገርህ ጻድቅ ሆይ ከችግርህ ለመላቀቅ ተስፋ አለህ የደረሰብህ ክፉ ነገር ዳግመኛ በእንተ ላይ ላይለለጥን አንድ ዋን አፉን ይዘጋልና ተጽናና።

ጸ ሎ ት አምላኬ ሆይ በትንሽ ፈተና ተስፋዩ እንዳይጨልምና ተስፋ እንዳልቆርጥ እርዳኝ።

የንባብ ክፍል ምሳሌ 3 1 12

## ሕጌን አትርሳ

«ልጄ ሆይ፡ ሕጌን አትርሳ፡ ልብህም ትእዛዜን ይጠብቅ፡ ብዙ ዘመናትና ረጅም ዕድሜ ሰላምም ይጨመሩልሃልና»

የኦሮ መመሪያ የሌላቸው ሰዎች «በወጣው ያውጣው» ማለት ያበዛሉ። ያገራቸው አስተዳዳሪዎች ያወጡትን ደንብና ትዕዛዝ ሲጥሱ፡ ከሁሉም በላይ የአምላካቸውን የእግዚአብሔርን ቃል ሲተላለፉ ሕሊናቸው ቅሬታ አይሰማውም።

እንደ እግዚአብሔር ሕግና ትእዛዝ የምንመላለስ ከሆነ የማይዘነፍ የሕይወት መመሪያ ይኖረናል። ስለዚህም ነው ዳዊት «የእግዚአብሔር ሕግ ፍጹም ነው፡ ነፍስን ይመልሳል፡ የእግዚአብሔር ፍርድ እውነትና ቅንነት በእንድነት ነው። ከወርቅና ከክቡር ዕንቁ ይልቅ ይወደዳል፡ ከማርና ከማር ወለላም ይጣፍጣል» የሚሰው።

በሕይወታችን በሚፈጸመው ነገር ሁሉ እግዚአብሔር እንዲመራን ከፈለግን በራሳችን ጥበብ ላንመካ፡ በራሳችን ማስተዋል ላንደገፍ፡ ከሀብታችንና ከፍሬአችን በኩራት ሁሉ ለእርሱ ባለማጂደል፡ በፍጹም ልባችን በእርሱ በመታመን መኖር አለብን።

የእግዚአብሔር ልጆች በሕጉና በትእዛዙ መራመድ ትተው መረን በሚሄዱበት ጊዜ፡ እግዚአብሔር ደግሞ ልጆቹን ለመገሰጽ ይገደዳል። እርሱ በጥፋታችንን ሲገስጸን በእሽታ መንፈስ ልባችንን በማቅናት በንስሐ መቀበል አለብን። ጌታም «እኔ የምወዳቸውን ሁሉ እገስጻቸዋለሁ እቀጣቸውማለሁ፡ እንግዲህ ቅና ንስሐም ግባ» ይላል። ራዕ 3 19

ጸ ሎ ት መታዘዝን ልማር ከቃልህ መንቀጥቀጥን ልማር በቃልህ መዋረድን ልማር በቃልህ



የንባብ ክፍል መዝ 94 1 23

## በአለኝታ የተሞላ ሕይወት

«እግዚአብሔር የረዳኝ በይሆን ነፍሴ ሰጥቂት ጊዜ በሲዖል በደረች ነበር» ቁጥር 17

አንድን ሰው ተደናቂ ከሚያደርጉት ጠባዮች አንዱ ባለበት የትምህርትም ይሁን የኦሮ ደረጃ መኩራራት ሳይሆን ከምን እንደተነሳና ማን ከዚያ እንዳነሳው በማስታወስ ራሱን ዝቅ በማድረግ ትሁት መሆኑ ነው። ይሁን እንጂ እንዲህ ዓይነቱን ተወዳጅ ባህርይ፡ «እኔነት» ዙፋኑን ዘርግቶ በተቀመጠበት በዚህ ትውልድ ውስጥ ማግኘት አስቸጋሪ ሆኖዋል። አንድ ታዋቂ ጋዜጠኛ እንዳሰው ይህ ትውልድ ራስ ወዳድ ትውልድ(The me generation) ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም ሲል ተናግሯል።

ዳዊትን እግዚአብሔር «እንደ ልቤ የሆነ» ብሎ ሲጠራው ከበቁት ምክንያቶች አንዱ ይህ የእግዚአብሔርን ውስታና ቸርነት ያለመዘንጋቱ ላይሆን አይቀርም። እግዚአብሔር ሲያነግሠው ከመቀባቱ አስቀድሞ ዙፋኑን ሰልጁ ሰሰሞን እስከወረሰበት ጊዜ ድረስ የግል ስደቶችና የጠላት ወራሪ ዳዊትን የመከራና የጦር ሰው አድርገውት ነበር። ከአረኝነት ጀምሮ እስከ ንጉሥነት ላጋጠሙት የትግል ምዕራፎችና ለገኛቸው ድሎች ለእግዚአብሔር በለውለታነቱን በመጥቀስ ይህ መለኮታዊ ጥበቃና የድል ኃይል በወቅቱ በይሰጠው ኖሮ የሚያየውን መከራ ሲያስታውስ «እግዚአብሔር የረዳኝ በይሆን ነፍሴ ሰጥቂት ጊዜ በሲዖል በደረች ነበር» ቁጥር 17 ብሎ ተናገረ።

አሁንም ቢሆን በፈተናችን ወቅት በራሳችን ጥበብ ወይም በምናውቃቸው ወዳጆቻችን ከመታመን ይልቅ «በክፉዎች ላይ ለእኔ የሚቆም ማን ነው? ዓመጸኛስ በሚያደርጉ ላይ ለእኔ የሚከራከር ማን ነው?» ቁጥር 16 ብለን እንደ ዳዊት ብንጠይቅ ቀደም በሉት ጊዜያት ከገጠሙን ፈተናዎች ነፃ ወዳወጣን አምላካችን ልበናችንን በማንሳት «እግዚአብሔር የረዳኝ በይሆን ነፍሴ ሰጥቂት ጊዜ በሲዖል በደረች ነበር» ቁጥር 17 ለማለት እንችላለን።

ጸ ሎ ት ጌታ ሆይ ውስታህን እንዳልዘነጋ እርዳኝ

የንበብ ክፍል ኢያሱ 1 1 19

## አትፍራ

«በምትሄድበት ሀሉ አምላክህ አግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነውና... አትፍራ» ኢያ 1፤9

በዚህ ዘመን የብዙ ሰዎች ልብ በፍርሐትና በድንጋጤ ይዝላል። የገንዘብ እጦት፡ የጤንነት ማጣት ከሰዎች ጋር ያለን ጎብረት መበላሸት በአጠቃላይ የኑሮ ውጣ ውረድ መንስዔ ሆኖ ልቦችን በጭንቀት ይወጠራል። ሆኖም እንድንፈራ የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም።

በዛሬው የንበብ ክፍላችን እንደምንመለከተው እግዚአብሔር ኢያሱን ሰለት ነገሮች ተናገረው።

1ኛ)ዮርዳኖስን ተሻግሮ ምድሪቱን እንዲወስድ ታዘዘ። በህሩ ሞልቷል፡መሸገርም ከበድ ነው እግዚአብሔር ግን ተሸገሩ ሊለው እናያለን። በሕሩን ቢሸገሩም በይሸገሩም ጠላቶቻቸው በዚያ አሉ። ቢሆንም እግዚአብሔር አሸናፊ አምላክ መሆኑን ተለማምደዋል።

ችግር ሊመጣ ግዙፍነቱንና ከበድነቱን እንመለከታለን፡ እንደነግጣለንም። የምናደርገው ነገር ይጠፋናል። ስለዚህም ችግራችንን እግዚአብሔር እንደሚፈታልን እንረሳለን። ችግራችንን ዛሬ እንዴት እናየዋለን? የእግዚአብሔርን አሸናፊነት ተለማምደናል?

2ኛ) ኢየሱ እንዳያወላውል ታዘዘ። መወላወል ለክርስትና ሕይወት ቀርቶ ለማንኛውም ተግባር አስፈላጊ አይደለም። ብዙ ጊዜ አንድ አቅጣጫ ይዘን የምንሠራው ሥራ መወረሸው ያማረ ይሆናል። ክርስትናም እንዲሁ ወደግራና ቀኝ የሚባልበት ሕይወት አይደለም። የድል አክሊላችንን ለመጎናጸፍ በቀጥታው እንጂዝ።

3ኛ) ኢያሱ ሕጉን እንዲጠብቅ ታዘዘ። ችግራችንን ለማሸነፍ እግዚአብሔር ከእኛ ሁለት ነገሮች ይፈልጋል፡ እነርሱም ማመንና መታዘዝ ናቸው።እኛም በእምነት በመታዘዝ ድነናል።

«ትጠብቅና ታደርግ ዘንድ በቀንም በሌሊትም አስበው።» ቃሉን ማሠላሰልና እርሱን መታዘዝ የብርታት ቁልፍ ነው። በእግዚአብሔርም መታመን የድንጋጤን ደመና ያስወግዳል።

ጸሎት ጌተ ሆይ፡ በችግሬ ውስጥ የአንተን ድምጽ ብቻ ልስማ።



የንበብ ክፍል « በሰዎችና በመላእክት ልሳን ብናገር ፍቅር ግን ከሌለኝ እንደሚጮህ ናስ ወይንም እንደሚንቧቧ ፅናጽል ሆኛለሁ። ትንቢት ቢኖረኝ ምስጢርንም ሁሉና ዕውቀትን ሁሉ ባውቅ ተራሮችንም እስከፈልስ እምነት ቢኖረኝ፡ ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ። » 1ኛ ቆሮ 13 1 2

## ፍቅር ከሌለኝ ከንቱ ነኝ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ በሚያስተምርበት ጊዜ ከትዕዛዛት ሁሉ የሚበልጠው የትኛው ነው ተብሎ ሲጠየቅ « ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ፡ በፍጹም ነፍስህ በፍጹምም አሳብህ ውደድ የምትለዋና ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ » የሚለው ነው ብሎ ይመልስላቸዋል። ከዚያም በማስከተል ከእነዚህ የምትበልጥ ሌላ ትዕዛዝ የለችም ብሎ ይደመድመዋል። (ማርቆስ 12 28)

ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮ ምዕ 13 ላይ እንደሚዘረዝረው ልዩ ልዩ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ታላቅ እምነት፡ መልክም ምግበር ወይንም ራስን ለሌሎች መስዋዕት አድርጎ ማቅረብ በፍቅር ከልተደረገ በዶና ውሜዊ ስርዓት ብቻ እንደሆነ አስረግጦ ይናገራል። እዚህ ላይ ልናስተውለው የሚገባን እነዚህ የተዘረዘሩት መንፈሳዊ የሚመስሉ ነገሮች ሁሉ ለውን መንፈሳዊ እንደማያደርጉ ብቻ ሳይሆን የመንፈሳዊነትም ምልክት እንዳልሆኑ ነው።

« ፍቅር የሌለው እግዚአብሔርን አያውቅም፡ እግዚአብሔር ፍቅር ነውና » 1ዮሐ 4 7

« ማንም እግዚአብሔርን እወዳለሁ እያለ ወንድሙን ቢጠላ ሐሰተኛ ነው ያየውን ወንድሙን የማይወድ ያላየውን እግዚአብሔርን እንዴት ሊወደው ይችላል።» 1ኛ ዮሐ 4 20 በማለት ሐዋርያው ዮሐንስም ስለ እውነተኛ ፍቅር የክርስትና ሕይወት መለኪያ በህርይ እንደሆነ የተናገረው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በለጠው መመሪያ ነው።

« እርስ በርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ ደቀመዛሙርቴ እንደሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚያ ያውቃሉ » ዮሐ 13 35

እኛስ የክርስቲያንነታችንና የመንፈሳዊነታችን መለኪያ ምን ይሆን? እኛስ ላይ አስቀድሞ የሚታየውና ምልክታችን አገልግሎታችን? ወይንስ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎቻችን? ወይንስ ለእግዚአብሔርና ለሰዎች ያለን እውነተኛ ፍቅር ይሆን?

ጸ ሎ ት

እግዚአብሔር ሆይ፡ አንተንና ሰዎችን በፍጹም ፍቅር እወድ ዘንድ በሰማያዊው ፍቅርህ ሙላኝ። አሜን!

በየቀኑ የሚነበብ የሰላሳ ቀናት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች December/1994

Dec 1 ዳን 8:1 27 1ዮሐ 2:1 17 መዝ 120:1 7 ምሳሌ 28:25 26

Dec 2 ዳን 921 11 1 1ዮሐ 2:18 3 6 መዝ 121:1 8 ምሳሌ 28:27 28

Dec 3 ዳን 11:2 35 1ዮሐ 3:7 24 መዝ 122:1 9 ምሳሌ 29:1

Dec 4 ዳን 11:36 12:13 1ዮሐ 4:1 21 መዝ 123:1 4 ምሳሌ 29:2 4

Dec 5 ሆሴዕ 1:1 3:5 1ዮሐ 5:1 21 መዝ 124:1 8 ምሳሌ 29:5 8

Dec 6 ሆሴዕ 4:1 5:15 2ዮሐ 1:13 መዝ 125:1 5 ምሳሌ 29:9 11

Dec 7 ሆሴዕ 6:1 9:17 3ዮሐ 1:14 መዝ 126:1 6 ምሳሌ 29:12 14

Dec 8 ሆሴዕ 10:1 14:9 ይሁዳ 1:25 መዝ 127:1 5 ምሳሌ 29:15 17

Dec 9 ኢዩ 1:1 3:21 ራእይ 1:1 20 መዝ 128:1 6 ምሳሌ 29:18

Dec 10 አሞጽ 1:1 3:15 ራእይ 2:1 17 መዝ 129:1 8 ምሳሌ 29:19 20

Dec 11 አሞጽ 4:1 6:14 ራእይ 2:18 3:6 መዝ 130:1 8 ምሳሌ 29:21 22

Dec 12 አሞጽ 7:1 9:15 ራእይ 3:7 22 መዝ 131:1 3 ምሳሌ 29:23

Dec 13 አብ 1:21 ራእይ 4:1 11 መዝ 132:1 18 ምሳሌ 29:24 25

Dec 14 ዮናስ 1:1 4:11 ራእይ 5:1 14 መዝ 133:1 3 ምሳሌ 29:26 27

Dec 15 ሚክ 1:1 4:13 ራእይ 6:1 17 መዝ 134:1 3 ምሳሌ 30:1 4

Dec 16 ሚክ 5:1 7:20 ራእይ 7:1 17 መዝ 135:1 21 ምሳለሌ 30:5 6

Dec 17 ናሆም 1:1 3:19 ራእይ 8:1 13 መዝ 136:1 26 ምሳሌ 30:7 9

Dec 18 ዕንባ 1:1 3:19 ራእይ 9:1 21 መዝ 137:1 9 ምሳሌ 30:1 9

Dec 19 ሶፎ 1:1 3:20 ራእይ 10:1 11 መዝ 138:1 8 ምሳሌ 30:11 14

Dec 20 ሐጌ 12:1 2:23 ራእይ 11:1 19 መዝ 139:1 24 ምሳሌ 30:15 16

Dec 21 ዘካ 1:1 21 ራእይ 12:1 13 1 መዝ 140:1 13 ምሳሌ 30:17

Dec 22 ዘካ 2:1 3:10 ራእይ 13:1 18 መዝ 141:1 10 ምሳሌ 30:18 20

Dec 23 ዘካ 4:1 5:11 ራእይ 14:1 20 መዝ 142:1 7 ምሳሌ 30:21 23

Dec 24 ዘካ 6:1 7:14 ራእይ 15:1 8 መዝ 143:1 12 ምሳሌ 30:24 28

Dec 25 ዘካ 8:1 23 ራእይ 16:1 21 መዝ 144:1 15 ምሳሌ 30:29 31

Dec 26 ዘካ 9:1 17 ራእይ 17:1 18 መዝ 145:1 21 ምሳሌ 30:32

Dec 27 ዘካ 10:1 11:17 ራእይ 18:1 24 መዝ 146:1 10 ምሳሌ 30:33

Dec 28 ዘካ 12:1 13:9 ራእይ 19:1 21 መዝ 147:1 20 ምሳሌ 31:1 7

Dec 29 ዘካ 14:1 21 ራእይ 20:1 15 መዝ 148:1 14 ምሳሌ 31:8 9

Dec 30 ሚል 1:1 2:17 ራእይ 21:1 27 መዝ 149:1 9 ምሳሌ 31:10 24

Dec 31 ሚል 3:1 4:6 ራእይ 22:1 21 መዝ 150:1 6 ምሳሌ 31:25 31

የዕለት ሲሳይ በየወሩ እየታተመ የሚወጣና በአብያተ ክርስቲያናት በኩል የሚሠራጭ የጥሞና ጊዜ መመሪያ ነው። ሆኖም በአከባቢያቸው ቤተ ክርስቲያን ለሌለ አማኞች ወይም በግል አድራሻቸው እንዲላክላቸው ለሚፈልጉ አንዲሁም በሥጦታ መልክ ለሌሎች ማበርከት ለሚወዱ አገልግሎት እንለጣለን።

ይህን አገልግሎት የሚሹ ከሆነ ከመመሪያው በስተጀርባ በሚገኘው አድራሻችን የሚከተለውን የገንዘብ መጠን ቢልኩልን መገልገል እንደሚችሉ በአክብሮት እንገልጻለን።

በዓመት፡

| | |
|---|---|
| USA | $18.00 |
| Canada | $30.00 |
| Ethiopia | $30.00 |
| Other | $35.00 |

አዘጋጆቹ